# የክርስቶስ ሞት እና የኃጢአት ይቅርታ ።

## "እርሱም የኀጢአታችን ማስተሰረያ ነው! 1ኛ ዮሐንስ 2፥2

የክርስቶስን ስቃይ መፅሐፍ ቅዱስ ባይዘግብልን ኖሮ ለመረዳት እጅግ የሚከብድ ነው ። አምላክ የሆነ ፣ በሰው ስጋ ያደር ፣ መሲህ ሆኖ የመጣ ፣ ክርስቶስ የተባለ ፣ ለሰው ልጆች ኃጢአት ሲል የተሰቃየ ፣ እንዲሁም የሞተ ። ይህ በጣም ለመረዳት የሚከብድ ነው ።ነገር ግን መፅሐፍ ቅዱስ ይህን በስርአት እና ቃል በቃል አስቀምጦልናል ።

በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ የክርስቶስ ሞት ተከስቷል ብቻ ሳይሆን የክርስቶስ ሞት ትርጉሙ ምንድነው ? የሚለውንም በግልጽ ያብራራልናል ። ክርስቶስ መስቀሉን ተሸክሞ ወደ ጎልጎታ ሲሄድ የተመለከቱ ሰዎች የተለያዩ ትርጉሞችን ሰጥተዋል ።

– ለእነ ቀያፋ ፖለቲካዊ ድርጊት ነው ብለው ያስባሉ ።

– ለጴንጤናዊው ጲላጦስ ሌላ ትርጉም አለው ።

– ለመቶ አለቃውም ሰውዬ ይህ የእግዚአብሔር ልጅ ነው ሲል ሌላ ትርጉም አለው ።

– በክርስቶስ ኢየሱስ ቀኝ እና ግራ ለተሰቀሉ ሰዎችም ሌላ ትርጉም አላቸው ።

ከዚያም ባሻገር ክርስቶስ ከሞተ ፣ ከተነሳና ካረገ በኃላ ላሉት ሁለት ሺ አመታት ውስጥ ለብዙ ሰነ መለኮታዊ ግምቶች ምክንያት (ምንጭ) ነው ።

ነገርግን ወደ ቅዱሳት መፅሐፍት ስንመለስ የክርስቶስን ስቃይ ታሪካዊ ክስተት ብቻ ሳይሆን – ትርጉሙንም ጭምር ያብራራልናል ። ታሪካዊ ክስተቱ በወንጌላት ውስጥ ተገልጧል ። ትርጉሙን ደግሞ በመልዕክታቶች ውስጥ በግልጽ ተገልጧል ።

### 1. የክርስቶስ ሞት ለኃጢአት ስርየት !

ማስተሰረያ – ማለት ይቅርታ ማስገኛ ማለት ነው ።

ነገርግን ጥያቄው ቃሉ የሚያገለግለው የኃጢአትን በደል በመደምሰስ የእግዚአብሔርን ቁጣ የሚያበርድ ? ወይስ የእግዚአብሔር ቁጣ በሌለበት ሰውን ከኃጢአት በደል ማንፃት ? በሌላ አገላለጽ ዋናው የመስዋቱ ውጤት የሚታየው በእግዚአብሔር አመለካከት ላይ ነው ወይስ በሰው ሁኔታ ላይ? ይህን ለመረዳት አጠቃላይ የቤዝሆትን ታሪክ መረዳት አለብን።

ከቃል ኪዳን ሥነ-መለኮት አንፃር የሰዎች ውድቀት አዳም "የሥራን ቃል ኪዳን" የመጣሱ ውጤት ነው። በመጀመሪያ እግዚአብሔር አዳምን የመለኮት መልክ ተሸካሚ እና የሰው ልጆች ሁሉ የቃል ኪዳን ተወካይ (የፌዴራል ራስ) አድርጎ ፈጠረው። እንደ እግዚአብሔር መልክ አዳም የተፈጠረው እግዚ አብሔርን እንዲወድና በእርሱ እንዲደሰት ነው። እግዚአብሔር በፍቅር በአዳም ልብ ላይ እግዚአብሔርን እና ሌሎችን እንዴት መውደድ እንዳለበት ያስተማረውን መልካም ሕጉን ጻፈ ( ሮሜ 2:14 )። እግዚአብሔር አዳም ከታዘዘ የዘላለም ሕይወትን እንደሚሰጠው ለአዳም ቃል ገባ (ዘፍጥረት 3:22 )፣ ነገር ግን አዳም ካልታዘዘለአዳም እና ለዘሮቹ ያለመታዘዝ የዘላለም ሞትን ማስጠንቀቂያ ሰጠ ( ዘፍጥረት 2:17 )። አዳም እግዚአብሔርን ባለመውደዱና ሕጉን በመጣሱ እግዚ አብሔርን ስላልታዘዘ፣ እግዚአብሔር አዳምን እና ከእርሱ የተወለዱትን ትውልዶች ሁሉ በዘላለም ሞት ረገማቸው።

በገነት ከአዳምና ከሔዋን ኃጢአት እንደምንመለከተው ኃጢአት የሰውን ልጅ ከእግዚአብሔር ይለያል። ፍጹም ታዛዥነት ብቻ የእግዚአብሔርን ፍትህ የሚያረካ ሲሆን ይህንንም አዳምና ሔዋን በአንድ ኃጢአት ከእግዚአብሔር ተለይተው እንደነበር እንመለከታለን። ገላትያ 3፡10 "በሕግ ሥራ የሚታመኑ ሁሉ በእርግማን በታች ናቸውና፤ በሕግ መጽሐፍ የተጻፈውን የማያደርግ ሁሉ የተረገመ ነው" ተብሎ ተጽፎአልና። የእግዚአብሔርን ትእዛዙት በሚተላለፉት ላይ እርግማን ይወርዳል፣ እና ማንም ነፃ አይወጣም ( ሮሜ. 3፡9-20, 23 )።

እግዚአብሔር ቅዱስ ነውና ለኃጢአት ቅጣት ያስፈልጋል ። ሕግን መጣስ እንዲሁ ትርጉም የለሽ እውነታ አይደለም፣ ምክንያቱም ኃጢአት በራሱ በእግዚአብሔር ላይ ማመፅን ይወክላል ( 1ኛ ዮሐንስ 3፡4 )። የኃጢአት ልብ እግዚአብሔርን አለማክበር እና እርሱን አለማመስገን ነው ( ሮሜ. 1፡21 )። ኃጢአት ለእግዚአብሔር ጌትነት ለመገዛት ግልጽ የሆነ እምቢተኝነትን ይወክላል፣ እና በትክክል ኃጢአት የሠሩ ሰዎች የእግዚአብሔር የቅጣት ፍርድ ይገባቸዋል። እግዚአብሔር ቅዱስ ነውና ( ዘሌ. 19፡2 ) ሕጉን በሚተላለፉት ላይ ይፈርዳል።

፨ የእግዚአብሔር ፍርድ በኖህ የጥፋት ውሃ፣ በብሉይ ኪዳን የአረማውያን ሕዝቦች ፍርድ፣ እና የእስራኤል የኃጢአቷ መፍረዱ ግልጽ ነው።

፨ መጥምቁ ዮሐንስ ሰዎች ከሚመጣው የጌታ ፍርድ እንዲሸሹ ያስጠነቅቃል ( ማቴ. 3፡1-12 )። መጪው ፍርድ ከመምጣቱ በፊት የሰው ልጆች ንስሐ እንዲገቡ ተጠርተዋል ( ሐዋ. 2፡14–39፤ 3፡12–26፤ 4፡8–12 )።

፨ ጳውሎስ ብዙውን ጊዜ የእግዚአብሔርን የመጨረሻ ፍርድ ይገልጻል እናም ሰዎችን በኃጢአታቸው ምክንያት ለዘላለም ለመቅጣት አምላክ "ጻድቅ" እንደሆነ ተናግሯል።

ሁሉም ሰዎች በቅዱሱ አምላክ ላይ ኃጢአት በመሥራታቸው ጥፋተኞች ስለሆኑ ምትክ ያስፈልጋቸዋል። ኃጢአት ሁሉ ቅጣት ይገባዋል ምክንያቱም ኃጢአት ሁሉ በራሱ በእግዚአብሔር ላይ ማመፅ ነው። የእንስሳት መሥዋዕቶች በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔርን ሕዝብ ኃጢአት ሲወስዱ፣ እነዚህ መሥዋዕቶች የሰውን ኃጢአት ሙሉ በሙሉ ማስተሰረይ አይችሉም።

ለዚያም ኢየሱስ ክርስቶስ በህዝቡ ቦታ በመተካት ወደ ምድር መጥቶ ሞተ፣ የሚገባቸውን ሙሉ ቅጣት በራሱ ላይ ተቀበለ። ክርስቶስ ህዝቡን ተክቷል ማለት– የህዝቡ ቅጣት በእሱ ላይ አርፏል ማለት ነው ።

ሮሜ 3፥25 "በደሙም በሆነው እምነት፣ እግዚአብሔር የማስተሰረያ መሥዋዕት አድርጎ አቅርቦታል። እግዚአብሔር ክርስቶስን የኃጢአት መሰዕዋት አድርጎ አቀረበው ሲል የኢንግሊዘኛው propitiation የሚልን ቃል ነው የተጠቀመው ።

የእግዚአብሔርን ቁጣ ለማቀዝቀዝ ወይንም ቁጣውን ለማርካት ማለት ነው ። ይህ አስቀድሞ በምዕራፍ 1:18 ያለውን የሚያመለክት ነው ። "በክፋታቸው እውነትን ዐፍነው በሚይዙ፣ በዐመፃቸውና በክፋታቸው ሁሉ ላይ የእግዚአብሔር ቍጣ ከሰማይ ይገለጣል፤" ሮሜ 1፥18 (አዲሱ መ.ት) በኃጢአታቸው ምክንያት ሊገለጥባቸው ያለው የእግዚአብሔር ፍርድ በኢየሱስ ላይ መገለጡን የሚያሳይ ነው ።

፨ በብሉይ ኪዳንም ደም የእግዚአብሔርን ቁጣ ያበርዳል ። አሮን እና ፊንሐስ የእግዚአብሔርን ቁጣ ለማብረድ ማስተሰረያ ሲያቀርቡ እናያለን ። ዘሆ 16:46-48ዘኍልቍ 16 (አዲሱ መ.ት) [46] ከዚያም ሙሴ አሮንን፣ "ከእግዚአብሔር (ያህዌ) ዘንድ ቍጣ ወጥቶ መቅሠፍት ጀምሮአልና ጥናውን ወሰደህ ዕጣን በመጨመር ከመሠዊያው እሳት አድርግበት፤ ፈጥነህም ወደ ማኅበሩ ሄደህ አስተሰርይላቸው" አለው።

[47] ስለዚህ አሮን፣ ሙሴ በነገረው መሠረት ወደ ማኅበሩ መካከል ሮጦ ገባ፤ መቅሠፍቱም ቀደም ብሎ በሕዝቡ መካከል መሰፋፋት ጀምሮ ነበር፤ ሆኖም አሮን ዕጣኑን ዐጥኖ አስተሰረየላቸው።[48] እርሱም በሕይወት ባሉትና በሞቱት መካከል ቆመ፤ መቅሠፍቱም ተከለከለ።

፨ እንዲሁም እግዚአብሔር ፍርድ ሊያደርግ ሲመጣ እስራኤላውያንን ያለፈው –የፈሰሰውን የእንስሳቱን ደም አይቶ ነው ።

ዘጸአት 12፥13 (አዲሱ መ.ት)  "ደሙም ያላችሁበትን ቤት ለይቶ የሚያሳይ ምልክት ይሆንላችኋል፤ እኔ ደሙን በማይበት ጊዜ እናንተን አልፋለሁ፤ ግብፅን ስቀጣ መቅሠፍቱ አይደርስባችሁም።"

## 2. ከህግ ርግማን ሊዋጀን ክርስቶስ ሞተ !

ገላትያ 3:13""በዕንጨት ላይ የሚሰቀል ሁሉ የተረገመ ነው" ተብሎ ስለ ተጻፈ፣ ክርስቶስ ስለ እኛ ርግማን ሆኖ ከሕግ ርግማን ዋጅቶናል፤" ገላትያ 3፥13 (አዲሱ መ.ት)

## ርግማን ምንድነው ?

እዚህ ጋር ጳውሎስ ርግማን ብሎ የፃፈውን የርግማን ጭብጥ – በድሮ ዘመን የነበረ አይሁዳዊ ለመረዳት እጅግ ቀላል ነው ። በእኛ ዘመን ግን ርግማንን ቶሎ ለመረዳት የሚቀለን– ጥፋትን ስናጣፋ ከእኛ በእድሜ የሚበልጥ ሰው የሚያወርድብን ክፋ ቃላትን ነው ። እኛ ርግማን የሚሰጠንን ትርጉም አይደለም አይሁዳውያን  የሚሰጣቸው ።

### በብሉይ ኪዳን እርግማን እንዴት ተገለፀ?

ዘዳግም 11 (አዲሱ መ.ት) [26] እነሆ፤ ዛሬ በረከትንና መርገምን በፊታችሁ አኖራለሁ፤[27] በረከቱ ዛሬ የምሰጣችሁን የአምላካችሁን የእግዚአብሔርን (ኤሎሂም ያህዌ) ትእዛዞች ስትፈጽሙ ሲሆን፣[28] መርገሙ ደግሞ፣ የአምላካችሁን የእግዚአብሔርን (ኤሎሂም ያህዌ) ትእዛዞች የማትፈጽሙ፣ የማታውቋቸውንም ሌሎች አማልክት ለመከተል እኔ ከማዝዛችሁ መንገድ የምትወጡ ከሆነ ነው።

እርግማን በብሉይ ኪዳን የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን አሉታዊ ፍርድ ነው ።  የበረከት ተቃራኒ ተደርጎ ነው የሚወሰደው ። እርግማን ከህጉ መስጠት እና ከኪዳኑ መመሰረት ጋር ነው የሚያያዘው ። የትኛውም ኪዳን አብሮት ስምምነት አለ። የኪዳኑን ግዴታዎች የሚጠብቅ ሽልማት ይጠብቀዋል ፣ ግዴታዎችን የሚጥስ ደግሞ ቅጣት ይጠብቀዋል ።   እርግማን እግዚአብሔርን በማይታዘዙና ቅዱስ ህጉን  በሚጥሱ ላይ የሚመጣ የእግዚአብሔር ፍርድ ነው ።

የርግማንን ትርጉም ይበልጥ ለመረዳት ከእርግማን ተቃራኒ ጋር ማያያዝ ወይንም ማነፃፀር አስፈላጊ ነው ።በረከትን መረዳት ይበልጥ እርግማንን እንድረዳ ያግዘናል ።

በዘፍጥረት ሰዎች በኤደን ገነት ውስጥ ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸው ግኑኝነት ከተቋረጠ በኃላ – በኤደን ገነት የነበራቸውን ያክል ግኑኝነት ባይሆንም ሰዎች በተወሰነ መጠንም ከእግዚአብሔር ጋር ይገናኙ ነበር ። ይህ ቢሆን ማንም የእግዚአብሔርን ፊት እንዲያይ አይፈቀድለትም ነበር። ይህ እግዚአብሔርን ማየት ለቤዝሆታችን ፍፃሜ ቀን የተጠበቀ ነው ። ያን ግዜ እግዚአብሔርን ፊት ለፊት እናያለን ! ይህ ለእኛ ተሰፋችን ነው ። ይህንንም የሚያሰረዳ እስራኤላውያን አንድ ቡራኬ አላቸው ። ካህኑ እስራኤላውያንን የሚባርክበት ቡራኬ ነው ።

ዘኍልቁ 6 (አዲሱ መ.ት) [24] " 'እግዚአብሔር (ያህዌ) ይባርክህ፤ ይጠብቅህም፤ [25] እግዚአብሔር (ያህዌ) ፊቱን ያብራልህ፤ ይራራልህም፤ [26] እግዚአብሔር (ያህዌ) ፊቱን ይመልስልህ፤ ሰላሙንም ይስጥህ።' "

የአይሁዳውያን ተሰፋ ይህ ነበር ።የእግዚአብሔር በረከት ለእነሱ የፊቱ መብራት ፣ ፊቱን ሲመልስ ወይን እስራኤላውያን እግዚአብሔርን ሲያዩት ነው!

እስራኤላውያን በረከትን በሚገባ ተረድተውታል ።

ተቃራኒው ደግሞ ርግማን ነው ። ከእግዚአብሔር ፊት መራቅ ፣ ከእግዚአብሔር መገኘት መራቅ ለእስራኤላውያን ርግማን ነው። ከእግዚአብሔር መገኘት ውጪ አንድ ጨለማ እንዳለ ያስባሉ ። ርግማን ከእዚህ የእግዚአብሔር መገኘት ርቆ ወደእዛ ጨለማ መጣል ነው ።

የማደርያው ድንኳን ሀሳብም ከዚህ ጋር የሚያያዝ ነገር አለው ። እግዚአብሔር ድንኳኑን ይመሰርታል ፣ በዚያ ድንኳን ዙርያ እስራኤላውያን ይኖሩ ነበር ። ነገርግን ወደ ውስጥ መግባት የሚፈቀድለት አንድ ሰው ብቻ ነበር እሱም ሊቀ ካህናቱ ነው ። እሱም በአመት አንድ ጊዜ በሰርየት ቀን ይገባል ። በሰርየት ቀን የሚፈፀመው ሰርአት ሁለት እንስሶችን ያካተተ ነው ።

የመጀመሪያው – የበግ ጠቦት ሲሆን – ሁለተኛው – የሚለቅ ፍየል (Escape goat) ነው።

ይህን የበግ ጠቦት ካህኑ ለህዝቡ ኃጢአት ሲል ይሰዋዋል። ፍየሉ ላይ ደግሞ እጁን በመጫን ምልክት እንዲሆን የህዝቡን ኃጢአት ሁሉ ፍየሉ ላይ ይናገርበትና ወደ በረሀ ይለቀቃል ። ይህም ከእግዚአብሔር መገኘት ውጪ ወዳለው ጨለማ ሄደ ፣ ከእግዚአብሔር ተለየ ፣ ተረገመ ማለት ነው ። የእስራኤልያዊያ ኃጢአት ያለበት ይህ ፍየል ከህያዋን ምድር ተቆረጠ ማለት ነው ።

## ይህ ድርጊት ከክርስቶስ ሞት ጋር ያለው ግኑኝነት።

**ይህ በአዲስ ኪዳን ውስጥ በግልጽ ተብራርቶ እናገኛለን ። የዮሐንስ ወንጌልን እንመልከት ።**

**ዮሐንስ 1:1 ላይ ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ጋር የነበረው ግኑኝነት በጣም አስፈላጊ ነው ። ለእግዚአብሔር ኢየሱስ ብቸኛ ሀብቱ ነው ። ልክ እንደዛሁ ለኢየሱሰም እግዚአብሔር ብቸኛ ሀብቱ ነው ። የእግዚአብሔር ደስታ ያለው በክርስቶስ ኢየሱስ ውስጥ ነው ። ኢየሱስንም የሚያስደስተው የአባቱ ደስታ ነው ። አባት ልጅን ይወዳል ልጅም ደግሞ አባትን ይወዳል። አባቴ ይወደኛል- አባቴን እወደዋለሁ ፣ የሚያደርገውን ሁሉ ያሳየኛል ፣ እቅድ ሲያወጣ ያሳየኛል የሚሉትን ቃላት ኢየሱስ በተደጋጋሚ ይጠቀማል ። በእግዚአብሔር ሀሳብ ውስጥ ልጁ ሳያውቅ አንዳች የምትሸከረከር ሀሳብ የለችም ። አንድም የምትጠነሰስ ሀሳብ የለችም ። “ከቶውንም እግዚአብሔርን ያየ ማንም የለም፤ ነገር ግን በአብ እቅፍ ያለው አንድያ ልጁ የሆነው አምላክ እርሱ ገለጠው።” ዮሐንስ 1፥18 ይህ የሚገልፀው በጣም ስለሚወደው ከአጠገቡ እንዲርቅ አይፈልግም በጣም ይወደዋል እያለን ነው ።**

**ይህንን ግኑኝነት አይሁዳውያን አላገኙትም ነበር ፣ ለእነሱ ይህንን ማግኘት በረከት ነበር ።**

**በጣም የሚገርመው ግን ከዛ ከከበረ ሰፍራ ወረዳ ። ኃጢአት የሌለበት በጣም ውብ የሆነ ቦታ ነው። ከእዚህ ፍቅር ፣ ከነገስበት ሰፍራ ከአባቱ እቅፍ ወጣ ። በጣም ቀዝቃዛ ወደሆነው አለም ነው የወረደው ። ከዛ ግን ለማን ነው የሞተው? ብዙሰዎችን ወደ ክብር ለማምጣት የሚታገለው ለነማን ነው ?? በጣም ክፉ ለሆኑ ሰዎች ፣ የአባቱ ጠላት ለሆኑ ፣ የአባቱን ክብር ላጎደፉ ሰዎችን ነው ። ይህ በጣም ታላቅ ውበት ያለው ታሪክ ነው ። እሱ ማድረግ ያለበት አባቱን የጎዱ ሰዎችን ማጥፋት ነው ። ልጅ የአባቱ መንግሰት እንዲነካ አይፈልግም ። የአባቱ መንግሰት ጠላቶቹን ሰይፍ ይዞ ነበር ማሰወገድ የነበረበት ።**

**ይህ አለም የእግዚአብሔር መቅደስ ማደርያ መሆን ነበረበት ፣ ነገር ግን ይህ አለም አሁን በኃጢአት የተያዘ ስለሆነ እግዚአብሔር በዚህ ማደር አይፈልግም ። የእግዚአብሔር ልጅ ይህንን ሊያፀዳ ነው የመጣው ። ኃጢአተኞችን ሊያሰወግድ ከዛ ንፁህ የሆነ አለም ለመፍጠር ማለት ነው ። ግን እኛ እንደምናሰበው በመግደል አይደለም ያፀዳው ። እራሱ በመሞት ነው ያፀዳው ፣ በእነሱ ፈንታ እሱ ደቀቀ።**

**እንደፀዳል የነበረው ፊቱ ከሰለ ። በጣም የከበረ ፊቱ በኃጢአት ምክንያት ከሰለ ። አባቱ ይህ ልጁ ነው ወይንስ ማነው እሰከሚል ድረሰ መልኩ ጠቆረ ። ኢየሱስ ይህንን ያደረገው ወደ አዲሱ መቅደሱ ሰዎች መግባት እንዲችሉ ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት (fellowship) እንዲያደርጉ የጥሪውን ካርድ ለመሰጠት ነው ።**

ዮሐንስ ይህ ሲገባው እንደዚህ አለ–

“ዮሐንስ በማግሥቱ፣ ኢየሱስ ወደ እርሱ ሲመጣ አይቶ እንዲህ አለ፤ “እነሆ! የዓለምን ኀጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ፤” ዮሐንስ 1፥29 (አዲሱ መ.ት)

## ማጠቃለያ

ኃጢአት ቀላል ነገር እንዳልሆነ ለመገንዘብ ኢየሱስን በመስቀል ላይ መመልከት በቂ ነው ። በሰው ልጅ ፣ በአምላክም ልጅ ላይ የፈሰሰው የእግዚአብሔር ቁጣ እንዴት ያላ ታላቅ ሚስጥር ነው ? እንዴትስ እናብራራዋለን ? በመስቀል ላይ የተሰራውን ሙሉ ለሙሉ ባንረዳውም ግን እንኪደውም።

የህይወታችን እና የዕውቀታችን ማዕከል ፣ የእግዚአብሔር ፍትህ እና ምህረት መገለጫ ፣ የሰዎች ደኅነት እና የፍጥረት መታደስ መሰረት ፣ የህያዋን ሁሉ ተስፋ የእግዚአብሔር ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ የመሰቀል ላይ ስራ ነው !

ጳውሎስ በገላትያ 2፡20 ላይ .......“ አሁንም በሥጋ የምኖረው ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን አሳልፎ በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለኝ እምነት ነው።” ይለናል

ለእኔ ከመጣ ፍርድ (ቁጣ) እኔን ዞር በል አለና ከኃላዬ ሁን ብሎ እራሱን አሳልፎ ሰጠ እያለ ነው ።

ለጳውሎስ መስቀሉ የዕውቀት ሁሉ መደምደሚያ ነው ።

“በመካከላችሁ ሳለሁ ኢየሱስ ክርስቶስን ያውም የተሰቀለውን፣ እርሱን ብቻ እንጂ ሌላ እንዳላውቅ ወስኜ ነበርና።” 1ኛ ቆሮንቶስ 2፥2 (አዲሱ መ.ት)

ክርስቶስ ሲሞት የቤተ መቅደሱ መጋረጃ ለሁለት ተቀዶ ነበር ይህ ግን ለምን ሆነ? መቅደሱ የእግዚአብሔር መገኛ ነበር ፣ ሰው በኃጢአት ምክንያት ከእግዚአብሔር መገኘት ስለራቀ መግባት አይችልም ነበር ፣ ነገር ግን ክርስቶስ የኀጢአትን ዕዳ በመክፈሉ ምክንያት ሰው እንደገና በእግዚአብሔር መገኘት ውስጥ መገኘት ይችል ዘንድ ክርስቶስ በመሰቀል ላይ ሰራው የመቅደሱን መጋረጃ ቀደደው ።

የመጋረጃው መቀደድ– አሁን ከልካይ የለውም ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ታርቃችኋል ፣ ጠብ ተወግዷል ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም ናችሁ ፣ እሱ አባታችሁ እናንተ ደግሞ ልጆቹ ናችሁ ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት ማድረግ ትችላላችሁ የሚል አዋጅ ነው ።

የኃጢአት ይቅርታን ከመሰቀሉ ካወጣችሁ - – ከክርስትና የሆነ የሰነ መለኮት ሀሳብ አይደለም የምታስወጡት ፣ ሙሉ በሙሉ ክርስትናን ነው ከህይወታችሁ የምታስወጡት ። ክርስቶስ ልንከፍለው የማንችለውን ዕዳ በመሰቀል ላይ ከፍሎታል !!

የጌታ ፀጋና ሰላም ከእናንተም ጋር ይሁን !

**አዘጋጅ ፡- ተካልኝ ኃ/ሚካኤል**